## ለታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ስለሚፈቅድ መመሪያ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ

## 1. መግቢያ

በአዲስ አበባ እና በሌሎችም ትላልቅ የአገራችን ከተሞች የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ከሚገኙት ተሽከርካሪዎች ውስጥ አብዛኛው ከ50 ዓመታት በላይ ያገለገሉ ናቸው። እነዚህ ተሽከርካሪዎች በእርጅና ብዛት አጥጋቢ የሆነ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑም በላይ ከፍተኛ የመለዋወጫ ቃፍላጎት እና የነዳጅ ፍጆታ ያላቸው በመሆኑ አገሪቱን ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ በመዳረግ ላይ ይገኛሉ።

የእነዚህ ታክሲዎች ባለቤቶችም ለመለዋወጫ ለነዳጅ ፍጆታ ከፍተኛ ወጪ የሚያወጡ በመሆኑ ከአገልግሎቱ የሚያገኙት ገቢ ኑሮቸውን በተገቢው መንገድ መምራት የሚያስችል አይደለም።

በሌላ በኩል በትላልቅ ሆቴሎችና በአውሮፕላን ማረፊያዎች የታክሲ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ተሽከርካሪዎች ወደ አገራችን ለሚመጡ ቱሪስቶች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የማያስችሉ በመሆኑ ቱሪስቶች በአገራችን ባለው የታክሲ አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ያሰማሉ።

እነዚህን ችግሮች በማስወገድ የከተሞችን ዕድገት የሚመጥን የታክሲ አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ በአሮጌ ተሽከርካሪዎች ምክንያት የሚከሰተውን የአየር ብክለት፣ የትራፊክ አደጋ፣ የውጭ ምንዛሪ ወጪ መቀነስ እንዲሁም በታክሲ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማሩ ዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል አዳዲስ ተሽከርካሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ረገድ ለታክሲ ባለንብረቶች የሚደረገው ድጋፍ ለአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች ተጨማሪ የገበያ ዕድል በመፍጠር ለእነዚህ ፋብሪካዎች መስፋፋት እንዲያግዝና ለዜጎችም ተጨማሪ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲያስችል ድጋፉ የሚደረገው ከአገር ውስጥ የተገጣጠሙ ተሽከርካሪዎችን ለመግዛት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

በመሆኑም መመሪያው በከተሞች አስፈላጊ የሆነ የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ የታክሲ እና የአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎችን ማስፋፋት ለማገዝ የሚያስችል ይሆናል።

## 2. የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱ ተጠቃሚዎች

የታክሲ አገልግሎት ሥራ የሚፈለገውን አገልግሎት በብቃት ለመስጠት የሚችለው በተደራጀ እና በተቀናጀ አኳኋን ሲመራ መሆኑ ግልፅ ነው።
ይህም በመሆኑ በመመሪያው ለታክሲ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተቋቋመው መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በታክሲ ባለንብረቶች ማህበር የተደራጁ ባለታክሲዎች ናቸው።

## 3. የመብቱ አጠቃቀም

